# የአንድነት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

# በሥልጣን መባለግ

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ. ም.

የአንድነት ፓርቲ ፕሮግራም ውስጥ የፓርቲው ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች በሚል ርእስ ስር የሚከተለውን ይላል፤ ---

***የፓርቲያችን ራዕይ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት ድህነት ተወግዶ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ብልጽግናና ፍትሕ የሰፈነባት ነጻ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የተመሠረቱባት፣ ለዓለም አቀፍ ሕዝቦች መልካም ግንኙነት የበኩሏን አስተዋጽኦ የምታደርግና የዜጎችዋ ሁሉ አለኝታና መኩሪያ የሆነች ኢትዮጵያን ማየት ነው።***

በአሁኑ ጊዜ የአንድነት ፓርቲ በጣም ከባድ መስዋእትነትን የሚጠይቁ ብዙ ሥራዎች በፊቱ ተደቅነዋል፤ የፓርቲውን አባሎች ማብዛት፣ ለፓርቲው ተልእኮ ማስፈጸሚያ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰብ፣ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መወያየትና ስለሚቀጥለውንም አገራዊ ምርጫ መነጋገርና እቅድ ማውጣት ጥቂቶቹ ናቸው:: በነዚህና በሌሎች መሠረታዊ የፓርቲ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ፋንታ የሥራ አስፈጻሚውን ትኩረት ሙሉ በሙሉ የያዘው በፓርቲው ውስጥ ሥልጣንን ማጠናከርና ውጭ ውጨን ማየት ነው። ይህንን መግለጫ ለአንድነት አባሎችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳወቅ የቆረጡ የአንድነት አባሎች የፓርቲውን መዋቅር ተከትለው በሕጋዊ ሥርዓትና በመግባባት መንፈስ የሥራ አስፈጻሚውን ትኩረት ወደፓርቲው መጠናከርና እድገት ለመሳብ የተቻላቸውን ሁሉ በተደጋጋሚ ሞክረው ያቃታቸው ናቸው:: ከነዚህም መሀከል የብሔራዊ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ሰብሳቢ የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የብሔራዊ ም/ቤት አባላት እንዲሁም ሌሎች አባላት ይገኙበታል።

## *መግቢያ*

ስሙ በግልጽ እንደሚያመለክተው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የተመሠረተው በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩ ባለቤትና የሥልጣን ምንጭ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ለማድረግ ነው:: ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስንልም የኢትዮጵያ ሕዝብ በልበ ሙሉነትና በነጻነት ሀሳቡን በፈለገው መንገድ እንዲገልጽና እንዲወያይ፣ እንደፈለገው በነጻነት እንዲሰበሰብና እንዲደራጅ ያለውን መብት ለማስከበር ነው:: ከዚህም ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትክክለኛ ሕጋዊ ሥርዓት ስር ያለምንም አድልዎ ኑሮውን እንዲመራና ሰብአዊ መብቶቹ በሙሉ የተከበሩበትን ሥርዓት ለመገንባት ነው።

ሊቀ መንበራችን ወይዘሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ በወያኔ/ኢሕአዴግ ወታደሮች ተይዘው ከታሰሩ በኋላና ኤንጂኒር ግዛቸው በወንበሩ ላይ በተጠባባቂነት ከወጡ ጀምሮ በሥራ አስፈጻሚው በኩል የተደረገው ገንቢ የሥራ እንቅስቃሴ በጣም ዝቅተኛ ነው:: የፓርቲው ገንቢ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት አብዛኛዎቹ በወጣቶች የተከናወኑ ናቸው:: የሚከተሉትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች እንመልከት፤ --

1. ስድስት የቃሌ ምሽቶች፣ ሁለቱ በሥራ አስፈጻሚው የተጠለፉ
2. የሥነ ጽሑፍ ምሽት
3. የሕዳር 27 2001 የመብራት ኃይል ሕዝባዊ ስብሰባ

4. ***ፅናት*** የሚባል ወርኃዊ መጽሔት መጀመር
5. ***ሰሙናይ*** የሚባል ሳምንታዊ ጋዜጣ መጀመር
6. አንድነት የተመሠረተበትን አንደኛ ዓመት በዓል ማክበር
    a. የ***ፅናት***ና የ***ሰሙናይ***ን የመጀመሪያ እትሞች ማውጣት
    b. በፎቶግራፍ ትርኢት ማዘጋጀት
    c. በፓርቲው ግቢ ውስጥ ለፓርቲው አባላት ስብሰባ በማድረግ
7. የሊቀ መንበራችንን ሕገ-ወጥ እስራት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ
8. ስለወይዘሪት ብርቱካን መታሰር ውይይት ማካሄድ ይገኙበታል።

ከእነዚህ ዝግጅቶች አብዛኞዎቹ የተፈጸሙት በወጣቶችና በሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴዎችና በኤዲቶሪያል ቦርዱ ትብብር እንጂ በሥራ አስፈጻሚው ትጋትና አመራር ሰጪነት አይደለም። እንዲያውም በነዚህ ዝግጅቶች ውስጥ የሥራ አስፈጻሚው ጣልቃ ሲገባ በሌላ ዓላማ እየተመራ የወጣቶቹንና የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ያዘጋጀውን ለማደናቀፍ ወይም ጠልፎ ለሌላ ዓላማ ለማዋል ነው። ለምሳሌ በሁለት የቃሌ ምሽቶች የሥራ አስፈጻሚው ጣልቃ ገብቷል፤ አንድ ጊዜ ከማንም ጋር ሳይነጋገሩ የራሳቸውን እንግዶች ከመድረክ ቡድን ጠርተው ምሽቱን ለመጥለፍ ሞክረዋል። ሁለተኛ ጊዜ ጠለፋው ሙሉ በሙሉ እንዲሳካላቸው ለማድረግ የቃሌን ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፓርቲው ግቢ አስወጥተው በኢምፒሪያል ሆቴል አድርገውታል። የአንደኛ ዓመት አከባበሩን ለማጨናገፍ በመድረክ መሪው ላይ የተሞከረው ራስን ከፓርቲው ዝግጅት በላይ አድርጎ በማሳበጥ በመድረኩ ላይ ስሜ በተሰየመው የመድረክ መሪ አይጠራ በማለት ተጽእኖ በማድረግ የበዓሉን ሥርዓት ለማደፍረስ መሞከር ከአንድ ከፍተኛ የፓርቲ መሪ (ያውም ከምክትል ፕሬዚደንት) የሚጠበቅ አይደለም። በፎቶግራፎች ትርኢትም ጊዜ ዋና ጸሐፊው ቢሮአቸውን ቆልፈው ብቅም ሳይሉ፣ ለወጉም ቢሆን ለፓርቲው ተጠባባቂ መሪ ክብር ብለው እንኳን ሳያጅቡ መቅረታቸው የኩርፊያቸውን ግለትና መጠን የሚያሳይ ነው። ሁለቱንም የፓርቲው አመራር አባላት ምን አስቆጣቸውና ለእንደዚህ ያለ የአደባባይ ቅሌት አበቃቸው? ብለን ብንጠይቅ ዝግጅቱ በእነሱ አመራር አነሳሽነት አለመሆኑ ብቻ ነው፤ ሌላ ምክንያት አይገኝለትም። በብቃት ማነስ፣ በበጎ ፈቃድና የአነሳሽነት መሪነት ጉድለት፣ ሥልጣናቸውን ለማደላደል ሲንደፋደፉ ጊዜ በማጣት ለፓርቲው እንቅስቃሴ ዝግጅቶቹን ለማካሄድ ባለመቻላቸው ምን ያበሳጫቸዋል። እንዲያውም ሌሎች ብቃት ያላቸው የፓርቲው አባላት በራሳቸው ተነሳሽነት፣ በራሳቸው ጊዜ፣ በራሳቸው ጉልበትና ገንዘብ የፓርቲውን እንቅስቃሴዎች ማዘጋጀታቸው አመራር ላይ ያሉትን ሰዎች ሊያስደስታቸው እንጂ ሊያበሳጫቸው አይገባም ነበር። ስንኩል አስተሳሰብ ጥሩ የሠሩትን ጥፋተኛ ያስደርጋል።

ከላይ የተገለጹትን የሥራ እንቅስቃሴዎች ጥቂት አባሎች በግል ትጋታቸውና በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት እየተገፉ ያከናወኗቸው እንጂ እንደሥራ አስፈጻሚው ፍላጎት ቢሆን አንዳቸውም በተግባር አይውሉም ነበር። ስለዚህም እነዚህ የአንድነት ፓርቲ እንቅስቃሴዎች በሥራ አስፈጻሚው ድጋፍ ሳይሆን ከሥራ አስፈጻሚው ጋር በመታገል የተፈጸሙ ናቸው። ሌሎች የታቀዱና በሥራ አስፈጻሚው የተጨናገፉ እቅዶች የሚከተሉት ናቸው፤ ---

1. ለአባሎች በስብሰባው አዳራሽ የትምህርት ውይይት
2. የክርክር ልምምድ
3. የንግግር ልምምድ
    ሀ. ተዘጋጅቶ በአንድ ርእስ ላይ ንግግር
    ለ. ሳይዘጋጁ በአንድ ርእስ ላይ በድንገት ንግግር

እነዚህን ዝግጅቶች ለመፈጸም አመራሩ ሲጠየቅ በኤንጂኒር ግዛቸው የተፈረመ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ገደቦች ይዞ ወጣ፤--

1. ስብሰባውን የሚጠራው አካል ማንነት
2. የስብሰባው ቀንና ሰዓት
3. የስብሰባው ዓላማና አጀንዳ

4. የስብሰባው ተሳታፊዎች ማንነትና ብዛት
5. ከጽ/ቤቱ የሚያስፈልጋቸው ድጋፍ

እንግዲህ ይህ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ያላነሰ መሰናክል ፈጠራ የፓርቲውን አባሎች ንቃተ ኅሊና በየጊዜው ከፍ ለማድረግ መጣር ያለበት ፓርቲ የሚያደርገው አይደለም:: ዝግጅቶቹ ለአባሎች ሁሉ ክፍት የሚሆኑና አመራሩም በፈለገው መንገድ እየተከታተለ ከፓርቲው ዓላማ የሚወጣ መስሎ ሲታያቸው አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ሲችሉ በቅድሚያ መሰናክል መፍጠር ቅን መንፈስን የሚያመለክት አለመሆኑ ግልጽ ነው:: የግል ሎሌነታቸው ካልተረጋገጠ በቀር ለፓርቲው የሚሠሩት ሁሉ በአመራሩ በኩል ዋጋ የሚያገኝ አይደለም፤ እንዲያውም አፍራሽ ተልእኮ ያላቸው በማስመሰል የተለያየ ስያሜ በመለጠፍ በተለይ ወጣቶቹን ተስፋ ለማስቆረጥ ብዙ ነገሮች በጋዜጣም ጭምር ተብሏል:: ወጣቶቹ ግን ተስፋ ሳይቆርጡ በራሳቸው ጊዜና በራሳቸው ገንዘብ በአንዳንድ በጎ ፈቃድ ባላቸው አባላት እየታገዙ እስከዛሬ የታየውን እንቅስቃሴ ሁሉ እያካሄዱ ናቸው::

## *የዋና ጸሐፊው ‹‹በድፍረት የመናገር›› አዋጅ*

*ሚያዝያ* 13 *ቀን* 2001 *ዓ.ም. ዋና ጸሐፊው ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ሰፊ ቃለ መጠይቅ ሰጥተው ነበር:: ስለፓርቲው አመራርና ስላለበትም ችግር በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ አስረድተዋል:: ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤* (በጉልህ የተጻፈው የእኛ አስተያየት ነው)

1. ዋና ጸሐፊው ደጋግመው ‹‹በድፍረት መናገር እችላለሁ›› ማለትን ይወዳሉ፤--**ለእውነት ክብር ካልሰጡ ድፍረት አይቸግርም፤**
2. ‹‹ፓርቲው ከተቋቋመ ገና ስድስት ወሩ ነው፤››--**እንዴት አድርገው ቢቆጥሩት ይሆን!**
3. ‹‹የብርቱካን ደጋፊ በመምሰልም ሆነ የሌሎች ባዕድ አካላት አቀንቃኞችና ወኪሎች በመሆን›› ፓርቲው ውስጥ ‹‹መተረማመስ›› የሚፈጥሩ ሰዎች በመኖራቸው ችግር እንዳለ፤--**ዋና ጸሐፊው የታወቁበት በድፍረትና በጭፍን ሰውን መወንጀል ነው:: በጋዜጣ ላይ ስለሆነ ድፍረታቸው ከድቷቸው ነው እንጂ ብቻ ለብቻ ሲናገሩ ስምም እየጠሩ ነው::**
4. ‹‹ፓርቲውን ለማሠራት የማይፈልጉ ሰዎች›› ለምክር ቤቱ መግለጫ ጽፈው ‹‹ውዥንብር›› መፍጠራቸው፤--**በሌላው ጊዜ ቢሮአቸውን ቆልፈው የሚቀመጡት አንሶ አባላት ለበዓል በተሰበሰቡበት ዕለት ቢሮአቸውን ቆልፈው የተቀመጡት ለሥራ ነው እንድንል ነው፤**
5. ‹‹እነዚህ ባዕድ የምልህ አካላት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የጻፍነው ደብዳቤ የመጀመሪያውን ድራፍት አይጋ ፎረም ለተባለ ድረ-ገጽ ልከውት›› ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ከመድረሱ ከሃያ አራት ሰዓታት በፊት ታተመ፤--**ምነው ራሳቸውን ቢጠይቁ! ሁሉም ነገር በጃቸው፤ ደንብንም የመሻር የፖሊቲካ ውሳኔ በጃቸው! ረቂቁን ለማስተላለፍ የፖሊቲካ ውሳኔ አድርገው ከሆነስ!**
6. ‹‹እንግዲህ አስቡት ከሴረኞች ጋር ቀን ከሌሊት እየታገልን ነው፤››--**በፓርቲው ውስጥ የሴራ ባለቤት ማን ሆነና!**
7. አንድ መዋቅራዊ ህልውና የሌለው አንድ ቡድን አለ፤...ፓርቲውን በፈለገው መንገድ ካላነቃነቅነው፣ ወደፈለግነው መንገድ ካልመራነው የሚሉ፣... የፓርቲውን ሕግና ደንብ ጠብቀው የተፈጠሩ ባለመሆናቸው ... ሰዎቹ የሚሄዱበት አቅጣጫ ትክክል አለመሆኑን ስለተረዳን ... አለመዋቅር አናነጋግርም ብለናል፤›› --**ጃኖ ወይም ካባ ያልለበሰ የፓርቲ አባል እሳቸውንም ካባ ያለበሰ ቢሆንም ዋጋ የለውም!**
8. ‹‹ዴሞክራሲያዊ ውይይትና ነጻ አሠራር የት አለ ቢባል በድፍረት አንድነት ፓርቲ ውስጥ እላለሁ፤››--**ድፍረቱን እንቀበላለን፤ ‹‹አናነጋግርም›› ብለው በሩን ከዘጉ በኋላ ዴሞክራሲያዊ ውይይትና ነጻ አሠራር! እንዴት ይሆን!**

9. ‹‹አንድ የፓርቲያችን የወጣት ቡድን ነኝ ብሎ ራሱን የሚጠራ ቡድን አለ፤›› **--እርስዎ ምን ይሉት ይሆን!**
10. ‹‹ራሳቸውን ሽማግሌዎች ነን ብለው የሰየሙ ቡድኖች…›› **--ለዴሞክራሲያዊ ውይይትና ነጻ አሠራር ዓይን አንሞላ አሉ! ሽማግሌውንም፣ ወጣቱንም ጠልተው የት ሊደርሱ ነው! ከጓደኞችዎ ጋር!**
11. ‹‹መድረክን ተቀላቅለን እንድንሠራ ማእከላዊ ምክር ቤት ነው በከፍተኛ ድምፅ የወሰነው፤ ›› **--አቤት! እግዚኦ! ሳይጸናብዎ ከእውነት ጋር ይታረቁ!**
12. ከፓርቲውም ይወጡና ‹‹በኢትዮጵያ ላይ ደባ የሚሠሩ ሰዎች፣›› ይላሉ፤**--በመድረክ ጉዳይ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ነው፤ ለወያኔ/ኢሕአዴግ ደጎንነት ማመልከትዎ ይሆን! እኛም ሌላ የምናውቀው አለ፤ ጊዜ ያወጣዋል፤ መሪ ማለት እንዲህ ነው!**
13. ‹‹የመጀመሪያውና ዋነኛው ችግር ባዕድ የሆኑ በፓርቲው ውስጥ በአመራር ደረጃ መገኘታቸው ነው፤ እነዚህ ባዕድ አካላት ፓርቲውን ለማፍረስና ለማተረማመስ የተሰገሰጉ ናቸው፤›› **--እርስዎን የመረጡዎት እነዚህ የተሰገሰጉ ባዕድ አካላት ይሆኑ! ሊበሏት የከጀሏትን መሆኑ ነው!**
14. ‹‹የፓርቲው ሕግ በጣም ጥብቅ የሆነ ነው…ይህ የፖሊቲካ ሥራ እንደመሆኑ መጠን አንዳንዴ ፖሊቲካዊ ውሳኔ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ፤ ሌሎችም ይህንን እንደሚጋሩኝ አምናለሁ፤…አለዚያ ደንብን የጠበቀ ውሳኔ የምንለው የት ያደርሰናል የሚለው አሳሳቢ ሆኖብናል፤ ፖሊቲካዊ ውሳኔ አሁን ለድርጅታችን ህልውና ወሳኝ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡›› **--ማሰብ እንዲህ ነው! ደርግም እንደርስዎ ቸግሮት ይሆን በፖለቲካ ውሳኔ ሰዎችን የረሸነው! እባብን የልቡን አይቶ …**

ከዚህ በላይ እየቀነጨብን ያወጣነውን ተመልክቶ ቃለ ምልልሳቸውን በሙሉ በማንበብ የዋና ጸሐፊውን እኩይ አስተሳሰብ ይበልጥ መረዳት ይቻላል፤ በተለይ ልብ ልንለው የሚገባን የአምባ ገነኖች ጠባይ የሆነውን በድፍረት ሰዎችን የመፈረጅና የማንኳሰስ ዝንባሌ ነው:: ለምሳሌ በሀሳብ የተለያቸው ሰው ‹‹ባዕድ›› ነው፤ ወይም ‹‹በኢትዮጵያ ላይ ደባ የሚሠሩ›› ናቸው፤ ወይም ‹‹ሴረኞች›› ናቸው፤ የአብዛኛዎቹ ጓደኞቻቸው አእምሮም በዚህ ዓይነት ሕመም የተገነዘ ነው፤ ለፓርቲው የሚያስቡትና በወገንነትና በባዕድነት የሚፈርጁት ባለሚዛን እሳቸው ብቻ፣ ኢትዮጲያዊ እሳቸውና ሎሌዎቻቸው ብቻ፣ ደንብን የመጣስና እንደልባቸው በዘፈቀደ በ‹‹ፖሊቲካ ውሳኔ›› ለመግዛት የሚፈልጉ እሳቸው ብቻ፣ ይህንን እኛ አንቀበልም:: ይህንን ብንቀበል ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር እንሆን ነበር፡፡ ከዚህ በታች በተጨባጭ ማስረጃዎች የምናረጋግጠው አመራሩ፣ በተለይም የምክትል ሊቀመንበሩና (ተጠባባቂ ሰብሳቢው) የዋና ጸሐፊው አመራር ብልሹ መሆኑን ነው፡፡

## *የአመራሩ የአሠራር ስልት*

ከላይ በበቂ ሁኔታ ለማስገንዘብ እንደተሞከረው የአንድነት ሥራ አስፈጻሚ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ የአንድነትን መሠረታዊ ዓላማ ፈጽሞ የሳተ የአመራር ስልት በመከተል ፓርቲውን በጣም የከፋፈለውና ወደአደገኛ ደረጃ ያደረሰው መሆኑን በግልጽ እያየን ነው፤ ይህ አመራር በሦስት የተዛቡ መሠረቶች ላይ እየተንከባለለ ነው::

1. በዘፈቀደ የጉልበት አሠራር በማስደንገጥና በማስበርገግ
2. የፓርቲውን ገንዘብ በመናኘት ታማኝ ሎሌዎችን መግዛት
3. በወዳጅነት/ጓደኝነት ጫና አብረው የሚቆሙትን ማሰባሰብ

እነዚህ ስልቶች በሙሉ ወያኔ/ኢሕአዴግ የሚጠቀምባቸውና የምንቃወማቸው ናቸው:: ከዚያም በላይ በፓርቲው ውስጥ ስንገባ የያዝነው ራእይ ይህ አይደለም፤ ስለዚህም በግል ከኤንጂኒር ግዛቸው ጋር በተለያዩ ጊዜያት ጉዳዮቹን እያነሣን፣ የፓርቲውን ዓላማና ደንቦች እየጠቀስን

መንገዳችንን እንዲያቃኑልን ደጋግመን ጠይቀናቸው ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ቆይተዋል:: እንዲያውም በጣም እየተበላሸ ወደመሄድ ላይ በመድረሱ በግድ ይፋ መውጣት አለበት ብለን ወስነናል።

## ሀ) የጉልበት አሠራር --- በሥልጣን መባለግ

1. ወይዘሮ ብርቄ ገዛኸኝ የሚባሉ በጽዳት ሠራተኛነት የተቀጠሩ ሴት በሕመም ምክንያት ለተወሰኑ ቀኖች በመቅረታቸው ያለምንም ማስጠንቀቂያና ካሣ በምክትል ጸሐፊው በአቶ መስፍን ፊርማ ከሥራ ተባርረዋል:: የቅጥሩን ደብዳቤ የፈረሙት ዋና ጸሐፊው አቶ ዓሥራት ጣሴ ሲሆኑ በቅጥር ደብዳቤው ላይ ቀኑ በትክክል አልተጻፈም፤ ስለዚህም የተቀጠሩበትን ትክክለኛ ቀን ለማወቅ አይቻልም፤ የተባረሩት ግን በየካቲት 25/2001 ነው:: ጉዳዩን በግልም፣ በምክር ቤትም በማንሣት እንዲታረም ለማድረግ የተደረገው ተደጋጋሚ ጥረት ሁሉ ሰሚ አላገኘም።
2. ወይዘሮ ሐና ዋለልኝ ለሊቀ መንበርዋ ጸሐፊነት ተቀጠሩ:: ትንሽ ቆይተው በዘፈቀደ አሠራር የአምስት ቋሚ ኮሚቴዎች ጸሐፊ አደረጓቸው:: አንድ ሰው ለአምስት ሰዎች እንዲታዘዝ ማድረግ የአስተዳደሩን ብልሹነትና ግዴለሽነት ያሳያል:: በዚሁ የተነሣ በተፈጠረ ውዝግብ በዋና ጸሐፊው በአቶ ዓሥራት ፊርማ የተቀጠሩት በምክትል ጸሐፊው በአቶ መስፍን ፊርማ ተባረሩ:: በግል ለኢንጂኔር ግዛቸው ሽፈራው፣ በምክር ቤትም ጉዳዩ ግልጽ የሰብአዊ መብትን የሚጥስ በመሆኑ እንዲታረም ደጋግመን በመናገራችን ያስገኘነው ውጤት የለም።
3. በአደራጅነት ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩ የቀጠና አደራጆችን ለአበል የሚሆን በጀት ስለሌለ ደመወዝ እንደማይከፈላቸው በደብዳቤ ተገለጸላቸው:: አባሎቹ ግን ፓርቲያችን ችግር ካጋጠመው ሁኔታዎች እስኪመቻቹም ሆነ እስከመጨረሻው ፓርቲያችንን በነጻ እናገለግላለን የሚል መልስ ሰጡና ሥራቸውን ቀጠሉ፤ ነገር ግን ለበጎ ፈቃደኛነታቸው የተሰጣቸው መልስ ንብረት አስረክበው ሥራ እንዲያቆሙ የሚል ነበር:: እንዲያውም ሰበብ ተፈልጎ አቶ አለባቸው አያሌው በደሴ ከተማ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ፈጽመዋል በሚል እገዳውን አጸኑባቸው:: አቶ እንዳሻው እምሻውን ደግሞ በነጻ ጉልበት ፓርቲውን እያገለገሉ ባሉበት ወቅት ግቢ እንዳይገቡ የዋና ጸሐፊው ቀኝ እጅ የሆኑት አቶ መስፍን ለጥበቃው ነግረው እስከመከልከል ደርሰው ነበር። ገና ከመጀመሪያው ዓላማው በበጀት ሰበብ ነጻ አባሎችን እያስወጡ ሎሌዎችን ለመደልደል እንደነበረ በግልጽ ይታያል።
4. አቶ ይልቃል ጌትነት የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቲ አባልና ጸሐፊ ነበሩ:: እሳቸው ባልነበሩበት በ14/8/2001 በተደረገ የድርጅት ጉደይ ቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አቶ ይልቃል ከጸሐፊነቱ ተሻሩ:: ከሳምንት በፊት (በ3/8/2001) በተደረገ የብሔራዊ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ በሥራ አስፈጻሚው ላይ አቶ ይልቃል የሰላ ሂስ ሰንዝረው አቶ መላኩ ደግሞ የሥራ አስፈጻሚውን አጥብቀው በመደገፍ ተናግረው ነበር:: ኢንጂነር ግዛቸው አቶ ይልቃልን በአቶ መልአኩ እንዲተኩ አደረጉ:: ሆኖም ከሦስት ቀን በኋላ አቶ መልአኩ በሌላ ጉዳይ ተጠርጥረው በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ውለዋል፤ ኢንጂነር ግዛቸውም ሆኑ ፓርቲው እስካሁን ስለአቶ መልአኩ መታሰር ያወጣው መግለጫ የለም:: እምነው ለድርጅት ጉዳይ ጸሐፊነት የሾሚቸው ሰው በግንቦት 7 አባልነት ተጠርጥረው ሲታሰሩ ፍርድ ቤት እስኪወስን ድረስ እንኳን የፓርቲው ድምፅ ሊሰማላቸው ይገባ ነበር፤ የራሳቸው ጉዳይ ነው በማለት ችላ የተባሉ ይመስላል:: አመራሩ የራሱ (የራስዋ) ጉዳይ ነው የማለት ልማድ ያደረበት ይመስላል።
5. አቶ አምኃ ዳኘውና አቶ ታምራት ታረቀኝ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ናቸው:: ነገር ግን ምሥጢር አወጡ ተብለው በሥራ አስፈጻሚው ታግደዋል:: በአንድነት ፓርቲ የዲሲፕሊን ደንብ 3.2/ወ በተደነገገው መሰረት ምሥጢር ነው የልተባለ ነገር እንደ ሚስጥር ሊቆጠር አይችልም:: በተጨማሪም ያልጸደቀ ቃለ ጉባኤ ውስጥ ያለውንና የሌለውን ማንም ስለማያውቅ በደፈናው ምሥጢር ማድረግ አይቻልም:: ሃሳባቸውን

የመግለጽ መብታቸውን ተጠቅመው በጋዜጣም ሆነ በሌላ መንገድ መግለጽ ምሥጢር አወጡ አያሰኝም:: ሰበብ መፈለግና ሌሎችን ጭጭ ለማሰኘት የታቀደ ነው::

6. የተለያዩ የሥራ አስፈጻሚ አባላት በተለይም ምክትል ሊቀ መንበሮቹና (ዶር.ኃይሉ አርአያ ሥራቸው ነው ቢባልም) ዋና ጸሐፊው በተለያዩ ጋዜጦች ገደብ የለሽ መግለጫ ሲሰጡ ቆይተዋል:: ማንም ይህንን መብታቸውን ለመጋፋት የሞከረ የለም:: አቶ አምኃና አቶ ታምራት ጋዜጣ ላያ መጻፋቸው ግን የሥራ አስፈጻሚውን እንደእግር እሳት ሲያንገበግባቸውና በፖሊቲካ ውሳኔ ሲያግዱና ለማባረርም ሲዘጋጁ ይታያሉ:: ሁለቱን አባሎች ለማስወጣት በስነ ስርዓቱ ደንብ መመሪያ 4.1 ላይ በግልጽ የተደነገገውን በመለወጥ ፓርቲውን ከሳሽ ሲያደርጉ የችሎታ ችግራቸውን ያሳያል:: ከዚህም በላይ ገና ክስን የመስማት ስልጣን ያለው የስነ ስርዓት ኮሚቴ ሳይቋቋምና በምክር ቤቱ ሳይጸድቅ እነሱ በግላቸው ያቋቋሙት ኮሚቴ ዳኝነት እንዲያይ ለማድረግ መሞከራቸው በስልጣን መባለጉ የደረሰበትን ከፍተኛ ደረጃ የሚያመለክት ተጨማሪ ማስረጃ ነው::
7. ምናልባትም በሥልጣን የመባለጉንና የማናለብኝነት አሠራሩን በግልጽ የሚያመለክተው የሥራ አስፈጻሚው በርካታ ስብሰባዎችን ሲያደርግ ሥርዓትን በያዘ መንገድ ቃለ ጉባኤ አይያዝም፤ ቃለ ጉባኤ እየተነበበ በስምምነት አይጸድቅም፤ አባሎቹ አይፈርሙበትም፤ የሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ የሚካሄደው በተዝረከረከና በዘፈቀደ ነው:: ይህ በቀጥታ የዋና ጸሐፊው ኃላፊነት በመሆኑ የችሎታና የብቃት ማነስን በጉልህ የሚያሳይ ነው:: በቅርቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጥያቄዎች ሲነሡ ያለምንም እፍረት ለሥራ አስፈጻሚው አባላት በርካታ ቃለ ጉባኤዎች የተባሉ ሰነዶች ለእያንዳንዳቸው እየተላኩ እንዲፈርሙበት ተጠይቀዋል:: ከዚህ የበለጠ የሥራ አስፈጻሚውን የኃላፊነት ስሜት ማጣት፣ የአሠራሩን ብልሹነት፣ ማናለብኝነትና ግዴለሽነት በገሀድ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም::
8. የፓርቲው ምክር ቤትን ጥያቄና ትእዛዝ የሥራ አስፈጻሚው በግዴለሽነት ያልፈዋል፤ በ9/8ና9/2001 በተደረገ የምክር ቤቱ ስብሰባ ከተቆርቋሪ አባላት በቀረበው ሰነድ ምክንያት አንድ አጥኚ ኮሚቴ ተቋቁሞ ውሳኔውን ለምክር ቤቱ አቀረበ:: በአጥኚው ኮሚቴ ሪፖርት ላይ ምክር ቤቱ በሰፊው ተወያይቶ ሀያ ሁለት የውሳኔ ሀሳቦችን አሳልፎ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከሁለት ሳምንት እስከ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ተግባራዊ አድርጎ ለምክር ቤቱ እንዲያሳውቅ አዘዘ:: ነገር ግን የሥራ አስፈጻሚው የምክር ቤቱን ስብሰባ የጠራው ከአንድ ወር ተኩል በኋላ ሲሆን ያም ራሱ የሥራ አስፈጻሚው በመረጠው አንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ለመነጋገር ሆነ:: ከዚያም በላይ ያለፈው ቃለ ጉባኤ ከተነበበ በኋላ በየትም ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅና ሥርዓትን ሁሉ በሚጥስ አሠራር ሎሌዎቻቸውን አሰልፈው በድምፅ ብልጫ ቃለ ጉባኤው ውይይት ተደርጎበት እንዳይጸድቅ አድርገው የስብሰባ ደንብንና ሥርዓትን በመሻር ወደሚያንገበግባቸው የመድረክ ጉዳያቸው ተንደርድረው ገቡ:: የምክር ቤቱ ሰብሳቢ አሠራሩን በመቃወም ስብሰባውን ጥለው ሲወጡ እንደገና ከሥርዓት ውጭ ሌላ ሰብሳቢ አስመርጠው ሕገ-ወጥ ዓላማቸውን ፈጸሙ::

## ለ) በፓርቲው ገንዘብ ታማኝ ሎሌዎችን መግዛት -- በሥልጣን መባለግ

ፓርቲው ገንዘብ የሚያገኘው ከአባሎቹና ከደጋፊዎቹ ነው፤ ስለዚህም በገንዘብ አወጣጡ ለአባሎቹና ለደጋፊዎቹ ኃላፊነት አለበት፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት ግዴታው ነው:: ገንዘብ እንዴት እንደሚሰበሰብ፣ ማናቸውም ግዢ እንዴት እንደሚፈጸም፣ ሠራተኞች እንዴት እንደሚቀጠሩና እንደሚሰናበቱ፣ ደመወዝ እንዴት እንደሚወሰን በግልጽ መታወቅ አለበት፤ በተወሰኑ ጊዜያትም የሂሳብ ምርመራ ተደርጎ ለምክር ቤቱ መቅረብ አለበት:: አለዚያ ጥቂቶች ሰዎች የብዙዎቹን

መዋጮ በዘፈቀደ የሚናኙበት ይሆናል። የፓርቲው ገንዘብ በግዴለሽነት እንደሚወጣ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል፤

1. የአንድነት መጽሔት ተዘጋጅቶ የማሳተሚያ ገንዘብ የለንም ብለው ለወራት ከቆየ በኋላ ለፓርቲው በጎ ፈቃድ ባላቸው ጥቂት አባላት ተነሳሺነት ብድር ተሰብስቦ ለመታተም ሲቃረብ አሥር ሺህ ብር (ከግማሽ በታች) ፓርቲው እንደሚያዋጣ ኢንጂኔር ግዛቸው መልካም ፈቃዳቸው ሆነ:: እሳቸው እንደሚሉትም በመጀመሪያ ለወጣው ከፍተኛ ግምት ገንዘብ የለም ተባለ እንጂ በኋላ ለቀረበው ግምት ከሃያ አስከሃያ አምስት ሺህ ብር ተይዞለት ነበር፤ ይህንን የሚያስተባብለው የመጨረሻውን የኅትመት ግምትና ከቅን አባሎች የተገኘውን ብድር ኤንጂኒር ግዛቸው ሲሰሙ በቂ ገንዘብ መኖሩንና ብድርም እንደማያስፈልግ በመግለጽ ፋንታ እሳቸውም በበጎ ፈቃዳቸው ከፓርቲው ገንዘብ ለፓርቲው መጽሔት አሥር ሺህ ብር እንዲሰጥ ወሰኑ።
2. የአንድነት መጀመሪያ ዓመት ሲከበር ለበዓሉ የመጡት እንግዶችና አባላት በኃይለኛ ጸሐይ ሲነፍሩ የዋሉት ድንኳን ለመከራየት ገንዘብ ባለመኖሩ መስሎን ነበር:: ነገር ግን በሰኔ 20 የቃሌ ምሽት ላይ የተጋበዙት ተናጋሪ ዶር. ነጋሶ ጊዳዳ ስለነበሩ ዝግጅቱን በኢምፒርያል ሆቴል ለማድረግ የሥራ አስፈጻሚው ችሏል:: ገንዘብ መውጣት አለመውጣቱ ብቻ ሳይሆን የሥራ አስፈጻሚውን የቁም-ነገር ሚዛን በጉልህ የሚያመለክት ነው:: በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚደረገው የአንድነት የልደት በዓል ይበልጣል? ወይስ በወር በወር የሚደረገው የቃሌ ምሽት? ከዚያም በላይ አስከዛሬ በአንድነት ጓሮ ሲደረግ የነበረው የቃሌ ምሽት በሰኔ ምን መና ወርዶለት ነው ኢምፒርያል የተደረገው? ለመሆኑስ ሥርዓትን ለመከተል ከተፈለገ የሥራ አስፈጻሚው በቃሌ ምሽት ዝግጅት ላይ ምን አገባው? ለዶር. ነጋሶ ክብር እንኳን ኢምፒርያልና ሸራተንም ቢሆን እንደማይበዛባቸው እናውቃለን:: ነገር ግን ዶር. ነጋሶ የአንድነት ዓመት ሲከበር የክብር ደረጃውንና ወጉን ሁሉ ትተው ከእኛው ጋር አብረው ቆመውና አብረው ተቀምጠው በጸሐይ ሲቃጠሉ ነበር፤ ስለዚህም የምናከብራቸውና ልናከብራቸውም የሚገባን ሰው ናቸው:: በዚያን ዕለት ለዶር. ነጋሶ ክብር ያላሰበው የሥራ አስፈጻሚ ከአንድ ሳምንት በኋላ ብልጭታውን ከየት አገኘው? ወደኢምፒርያል ሆቴል የተፈጸመው ሽርተቴ በዶር. ነጋሶ ሰበብ በአንድነት ግቢ ውስጥ በሥርዓት በተሰየመው ኮሚቴ የተዘጋጀውን ለማደናቀፍ እንደነበር ለመገመት አዳጋች አልነበረም፤ ግን ዶር. ነጋሶን ይዘዋቸው ባይወርዱ መልካም ነበር።
3. የፓርቲውን አንደኛ ዓመት ለማክበር የተዘጋጀው አንዱ የፎቶግራፎች ትርኢት ነበር፤ ፎቶግራፎችን ለማሰባሰብና በሰፊው ለማዘጋጀት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በገንዘብ እጥረት ምክንያት መጠነኛ ሆኖ ተከናወነ:: ይህ የተከናወነው በጎ ፈቃድ ያላቸው አባሎች ባዋጡት ገንዘብ እንጂ በፓርቲው አመራር በኩል የተደረገ አስተዋጽኦ አልነበረም።
4. የማይፈልጓቸውን ሰዎች በዘፈቀደ የሚያባርሩትን ያህል የሚፈልጓቸውን ሰዎች በዘፈቀደ ይቀጥራሉ:: የደመወዝ አመዳደባቸው የትምህርትም ሆነ የልምድ ችሎታን የሚያመለክት አይደለም:: እንዲህ ያለ በማስፈራራትና በመደለል ታማኝ የግል ሎሌዎችን የማሰባሰብ ዘዴ እየታየ ነው::
5. በደብረ ማርቆስ ሕዝባዊ ስብሰባ ለመገኘት የሚሄዱትን አባሎች ወስዶ የሚመልስ አሥራ ሁለት ሰዎችን የሚይዝ መኪና ፓርቲው ተከራይቶ ነበር:: በመሄጃው ቀን ኢንጂኔር  ግዛቸው በግል ፍላጎታቸው ብቻ አቶ ደበበን ከለከሉ:: አቶ ደበበ የፓርቲው የኅትመት ዝግጅት ቦርድ ሊቀ መንበር ናቸው:: ፅናት የሚባለው ወርኃዊ የፓርቲው መጽሔትና ሰሙናይ የሚባለው የፓርቲው ሳምንታዊ ጋዜጣ በአቶ ደበበ የተግባር ኃላፊነት ውስጥ ነው:: አቶ ደበበን ከደብረ ማርቆስ ለማስቀረት ኢንጂኔር ግዛቸው የሰጡት ምክንያት ሌሎች ጋዜጠኞች አሉን የሚል ነበር:: ኢንጂኔር ግዛቸው በፓርቲው ገንዘብ በተከራዩት መኪና የውጭ ጋዜጠኞችን ለማመላለስ ሲፈቅዱ የፓርቲውን ጋዜጣ

የሚያዘጋጁትን መከልከላቸው ምንም አሳማኝ ምክንያት የማይገኝለት የማናለብኝ አሠራር ነው:: በመጨረሻም በፓርቲው ገንዘብ ለአሥራ ሁለት ሰዎች የተከራዩትን መኪና ለስምንት ሰዎች ብቻ ተጠቅመውበታል።

6. ከአባሎች መሀከል ፎቶገራፍም ሆነ ቪድዮ የማንሣት ችሎታ ያላቸው ሰዎች መኖራቸው እየታወቀ ከፓርቲው ውጭ እየቀጠሩ ያሠራሉ።

## ሐ) በወዳጅነትና በታማኝነት አብረው የሚቆሙትን ማሰባሰብ --- በሥልጣን መባለግ

በፓርቲው ውስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች ምንም እንኳን ለአገራቸው አንድ ዓይነት ዓላማ ያነገቡ ቢሆንም በብዙ መንገድ የተለያዩ አመለካከቶች ያላቸው ናቸው:: እነዚህን የተለያዩ አመለካከቶች ለአንድ ዓላማ እንዲሰለፉ ለማሳካት እንዲቻል ኃላፊነቱ የተጣለው በአመራሩ ላይ ነው:: በተቃራኒው አመራሩ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች በማወያየትና በማከራከር ሀሳቦች እንዲጠሩ በማድረግ ፋንታ ለአመራሩ የሚመቹ ሰዎችን በዙሪያው በማሰባሰብ ፓርቲውን ለመቆጣጠር ሲሞክር አባሎቹ ሁሉ የቆሙለትን የዴሞክራሲ ዓላማ ወደጎን በመተው ወደአምባገነንነት ያዘነብላል፤

1. በደብረ ማርቆስ ችግር በመከሰቱ የድርጅት ጉዳይ ኮሚቴ በ27/9/2001 በተደረገው ስብሰባ ችግሩን የሚፈታ ቡድን እንዲሄድ በቃለ ጉባኤ ወሰነ:: በማግስቱ ጠዋት አበል ለመቀበል ወደ ቢሮ የመጡት የቀጠናው አስተባባሪ ኃላፊ አቶ ይልቃል ጌትነት የተመረጡት አባላት ቀርተው በምትኩ አቶ ልባይ አበበ ከእሳቸው ጋር እንደሚሄዱ ተነገራቸው፤ በቃለ ጉባኤ የተወሰነው በቃል ትዕዛዝ ተሽሮ ፕሮግራሙ መቋረጥ ስላልነበረበት በ29/9/2001 ወደ ቦታው ተጓዙ። በመሠረቱ አቶ ልባይ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባል አንጅ የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባል አይደሉም::
2. አቶ ንጉሤ ነውጤ የሕግና ሥነ ሥርዓት ቋሚ ኮማቴ ስብሳቢ ናቸው፤ ነገር ግን በኢንጂኔር ግዛቸው ትእዛዝ በድርጅት ጉዳይ ሥራ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የክፍለ ከተማዎችን ሥራና የመሃል ኢትዮጵያን ሥራ እያወኩ ይገኛሉ፤ ከዚያም በላይ የሕግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴውን ወደከሳሽና ፍርድ ሰጪነት እንዲለውጡት እየተገፉ ናቸው።
3. አንድ ሰው ብቻ የፓርቲው ገንዘብ ተቀባይ፤ የፓርቲው ግምጃ ቤት፤ የፓርቲው ግዢ ክፍል ኃላፊ ነው:: ትክክለኛ አስተዳደር ቢኖር እነዚህ ሥራዎች በአንድ ላይ የአንድ ሰው ኃላፊነት ሊሆኑ አይችሉም ነበር።
4. እስካሁን ድረስ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳይፈጽም የሥራ አስፈጻሚው እንቅፋቶች እያበዛበት ነው።
5. የሥራ አስፈጻሚው በየሦስት ወር ለምክር ቤት የሥራ ክንውኑን ማቅረብ ሲገባው እስካሁን አላደረገም።
6. በሥራ አስፈጻሚው ውስጥ የተለመደውን በቡድን ድምፅ የመስጠት አሠራር በምክር ቤቱም ውስጥ በማስለመድ የፈለጉትን ጉዳይ እንደኢትዮጵያ የተወካዮች ምክር ቤት ዳምጠው ያሳልፋሉ።

## *መደምደሚያ*

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ አባሎች ሁሉ የፓርቲያቸውን ራእይ፣ ዓላማና ደንቦች ለማስጠበቅ ነቅተው መተባበር አለባቸው:: አሁን በተያዘው የተንኮል፣ የሐሰት፣ የመደለል ወይም የማስፈራራት መንገድ ወደዓላማችን እንደማንደርስ በጣም ግልጽ ነው:: በጥቂት ሰዎች የተንኮል ትጋት የኢትዮጲያን ሕዝብ ተስፋ ለሁለተኛ ጊዜ እንዳናጨልምበት በቆራጥነት መጠየቅና እውነቱን ፈልፍሎ ማውጣት ግዴታችን ነው:: የአንድነት ዓላማ ፓርላማ ያሉትንም ሆነ ወደፓርላማ ለመግባት ያኮበኮቡትን እያጨበጨቡ ለማጀብ ሳይሆን ለነጻነት፣ ለፍትሕና ለእኩልነት የሚታገሉ

አባሎችን ለማፍራት ነው:: በሙሉ ልባቸው በሰላማዊ ትግል ዓላማችንን ለማሳካት የሚጥሩ እንጂ ከትግል በፊት እጅ የሚሰጡ መሪዎቸን አንሻም፤ በአባሎች መዋጮ እየኖሩ እነዚያኑ አባሎች በአደባባይ የሚወነጅሉ መሪዎችን ልናምናቸው አንችልም:: የሀሳብ ልዩነትንና ክርክርን እንደጦር የሚፈሩና በሀሳብ የሚለዩአቸውን እንደጠላት የሚመለከቱ መሪዎች ፖሊቲካ ምን ማለት እንደሆነ አልገባቸውም፤ በካድሬነታቸው የተጫኑትን ጭፍን አሠራር ገና አላራገፉም፤ ምሥጢሩ ለገባው የኢትዮጵያ ሕዝብ **እንኳን ይቺንና የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን** እያለ የሚተርት ነው፤ አይናቅም፤ በብልጣብልጥነት አይነዳም።

በጥቅማጥቅምና በወዳጅነት የተነሡለትን ዓላማ ለዘነጉትና በጥቅማጥቅም ለተያዙ አባሎች ሁሉ ቆም ብለው እንዲያስቡና ወደኅሊናቸው ተመልሰው ነጻነታቸውን እንዲያስቀድሙና በቃል ኪዳናቸው መሠረት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቆሙ አደራ እንላቸዋለን:: ለእውነት ቆመናልና አብራችሁን ቁሙ።

እስከዛሬ በትእግስት ፊት ለፊት በመነጋገርና በውይይት ችግሮቹን ሁሉ እንፈታለን በማለት ዋና ጸሐፊው የራሳቸውን ሥራ አስተኝተው የሕዝብ ግንኙነቱን ሥራ ነጥቀው በየጋዜጣው ከእውነት ጋር የማይዛመዱ ነገሮችን ሲገልጹ ዝምታን መርጠን ቆይተናል፤ ከዚህ በኋላ ዝም አንልም።

| ተ.ቁ. | ስም | በፓርቲው ውስጥ ያላቸው ሀላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም | የብ/ም/ቤት አባል |
| 2 | ዶ/ር ሽመልስ ተ/ጻዲቅ | የብ/ም/ቤት ሰብሳቢ |
| 3 | አቶ ውሮታው ዋሴ | የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ሰብሳቢ |
| 4 | አቶ አመሃ ዳኘው | የብ/ሥ/አስፈጻሚ አባል የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ |
| 5 | አቶ ታምራት ታረቀኝ | የብ/ሥ/አስፈጻሚ አባል የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ |
| 6 | አቶ ደበበ እሸቱ | የኤዲቶሪያል ቦርድ ስብሳቢ |
| 7 | አቶ ይልቃል ጌትነት | የብ/ም/ቤት አባልና የሰሜን ቀጠና ኃላፊ |
| 8 | አቶ የሺዋስ አሰፋ | የብ/ም/ቤት አባልና የወጣቶች ጉዳይ ም/ሰብሳቢ |
| 9 | አቶ ፋኑኤል ደጌ | የብ/ም/ቤት አባል |
| 10 | አቶ አለባቸው አያሌው | የብ/ም/ቤት አባል |
| 11 | ወ/ት ሃና ዋለልኝ | የብ/ም/ቤት አባል |
| 12 | ወ/ት ትዕግስት ተሾመ | የብ/ም/ቤት አባል የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አባል |
| 13 | አቶ ጌታነህ ባልቻ | የአራዳ ክ/ከ/ህ/ግ/ሀላፊ የጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ፀሃፊ |

| | | |
|---|---|---|
| 14 | አቶ ሰይድ ኢብራሂም | የየካ ክ/ከ ሰብሳቢ |
| 15 | አቶ ብረሃኑ መሰለ | የየካ ክ/ከ ም/ሰብሳቢ |
| 16 | አቶ ስለሺ ሐጎስ | የህዝብ ግ/ አባል እና የሰሙናይ ጋዜጣ አዘጋጅ |
| 17 | አቶ እንዳሻው እምሻው | የመህል ኢትዮጵያ ቀጠና ፀሃፊ |
| 18 | አቶ አንተነህ ማስረሻ | የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ፀሃፊ |
| 19 | አቶ አርአያ ጌታቸው | የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባል እና የሚዲያና ኮምኒኬሽን ሰብሳቢ |
| 20 | ወ/ት ኤልሳቤጥ ወሰኔ | የወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባል እና የማህበራት ጉዳይ ሰብሳቢ |
| 21 | ወ/ት ርዕዮት አለሙ | የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አባል |
| 22 | | |
| 23 | | |
| 24 | | |
| 25 | | |
| 26 | | |
| 27 | | |
| 28 | | |
| 29 | | |
| 30 | | |
| 31 | | |
| 32 | | |
| 33 | | |
| 34 | | |
| 35 | | |

| | | |
|---|---|---|
| | | |